የደቀ መዝሙርነት መርሖዎች

# የትምህርቱ መሰረታዊ ሃሳቦች

## የወንጌል ስርጭት መንደርደርያ

### ትምህርት 8፡የወንጌል እዉነተ ምንድን ነዉ

– የሃጥያት ችግር

የአዳም ሃጥያት በሁሉም የሰዉ ዘረ ላይ ነበር ተጽእኖዉን ያሳረፈዉ። ነገር ግን ኢየሱስ የእርሱ ጽድቅ የአዳም እና የእኛን የኃጢአት ዋጋ በራሱ ላይ ወስዷል። ይህ ትምህርት የሃጥያት ጽንሰ ሃሳብ በወንጌል መልእክት ዉስጥ አስፈላጊዉ ክፍል እንደሆነ ትረዳ ዘንድ ያግዝሃል። ሌሎችን በተሳካ ሁኔታ ታስተመር ዘንደ ስለእዚህ ጽንሰሃሳብ አንብብ።

ወንጌል ሰዉን ወደ እግዚአብሄር ለመሳብ እና ሃጥያቱ ይስተሰረይለት እና የዘላለም ህይወት ይኖረዉ ዘንደ ነበር የተጻፈዉ። ወንጌል አስፈላጊነቱ እስካሁን ድረስ የቀጠለዉ ለዚህ ነዉ።

ወንጌሉ የተፃፈው ሰውን ወደ እግዚአብሔር ለመሳብ ነው ። ይህን ተከትሎም የኃጢያትን ይቅርታ እና የዘለአለማዊ ህይወት ስጦታን ይቀበላል።

ቃል በቃል ሲተረጎም ወንጌል ማለት መልካም ዜና ማለት ነዉ። ዛሬ ዛሬ የብዙሃን መገናኛዎች በአስጨናቂ ታሪኮች እና በአፈራሽ ዜናዎች በተጨናነቁበት ወቅት እና በህይወታችን ዉስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ በምናልፍበት ግዜ ከምንግዜዉም በላይ የጥሩ ዜና የምንፈልግበት ወቅት ላይ ያለን ይመስላል።

የመልካሙ ዜና ጸሃፊ እግዚአብሄር ነዉ። የሰዉ ልጅ ከሃጥያቱ እንዴት ሊድን እንደሚችል፤ ማን ሊያድነዉ እንደሚችል፤ ይህ እንዴት ሊደረግ እንደሚችል እና ይህ መልካም ዜና እንዴት ለሰዉ ዘሮች በሙሉ ሊዳረስ እንደሚችል አቅዶታል። ከዚህም በላይ የተጻፈዉ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ በኩል በእግዚአብሄር የተቀኘ እንደሆነ እናምናለን። ስለእዚህ ጓደኞቻችንን በምናገኘ ግዜ ወንጌል ከእግዚአብሄር እንጂ ከሰዉ ልጅ እንዳልሆነ መንገሩ በጣም ጠቃሚ ነዉ። ሃዋሪያዉ ጳዉሎስ በገላቲያን 1 ፡ 11-12 ‘ወንድሞች ሆይ፥ በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ አስታውቃችኋለሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትምም።’

መጽሃፍ ቅዱስ የተጻፈዉ የሰዉን ልጅ ወደእግዚአብሄር ለመሳብ ነዉ። ይህም በየአቅጣጫዉ ያሉ የሰዉ ዘሮች ለሃጥያታቸዉ ይቅርታን እና የዘለአለም ህይወትን ያገኙ ዘንድ ነዉ። መጽሃፍ ቅዱስ ለአንዳንድ የህይወት ጥያቄዎች እንደ የሰዉ ልጅ አመጣጥ፣ የሃጥያት ምንጭ እና ምክንያት እንዲሁም ስለመዳን ትርጉም ግልጽ የሆነ መልስ ይሰጣል።

እግዚአብሄር ሰዉን የመፍጠር አላማዉን እነመልከት። የዮሃንስ ራእይ ፬:፩፩ እና ትንቢተ ኢሳያስ ፬፫:፯ እንደሚያመለክተን ሰዉ ለእግዚአብሄር ደስታ እና ድል ሲባል የተፈጠረ ነዉ። በእርግጥ እግዚአብሄር አዳምን እና ሄዋንን በአምሳሉ ከፈጠረ በሁዋላ በመሬት ላይ ሙሉ ስልጣንን ሰጥቱዋቸዉ ነበር (ኦሪት ዘፍጥረት ፩ : ፪፮-፪፰ ተመልከት)። በእርግጥ የእግዚአብሄር ዘላለማዊ አላማ የነበረዉ የሰዉ ልጅ እርሱን በምድር እንዲወክል እና ሰለድሉ እንዲኖር እንደነበር ግልጽ ነዉ። አዳም እና ሄዋን የእግዚአብሄርን ፍቅር እና ጥበቃ ከማጣጣማቸዉም በላይ ለየትኛዉም ፍላጎታቸዉ እርሱን ነበር የሚሞረኮዙት። እግዚአብሄርም የተትረፈረፈ ህይወት ከመስጠትም በላይ ራሱን በሁሉም ደሎቹ ማለትም በቅድስናዉ እና በጽድቁ ገልጾላቸዉ ነበር።

ነገር ግን የተከለከለዉን ፍሬ በመብላት ከእግዚአብሄር ተዛዝ በወጡ ገዜ በመንፈስም (ኦሪት ዘፍጥረት ፫ ፡ ፩-፯) ቆይቶም በአካል ( ኦሪት ዘፍጥረት ፰ ፫-፰) ከእግዚአብሄር ተነጠሉ። በእንዲህ ባለ መልኩም ሃጥያት ወደአለም ገባ። ፈጹም በሆነዉ አለም አዳም እና ሄዋን ሃጥያትን መረጡ። ከዛን ገዜ ጀምሮ ሃጥያትም የሰዉ ልጅ ተፈጥሮ አካል ሆነ። ሁላችንም በእዚህ ሃጥያት ዉስጥ ነዉ የተፈጠርነዉ።

የሌላ ሃይማኖት ተከታታይ ለሆኑ ጓደኞቻችን የሃጥያትን ምንጭ ማስረዳቱ በጣም ጠቃሚ ነዉ። ምክንያቱም ስለክፉ ነገር እና ስለ ክፋት ለማስረዳት ጥሩ መንደርደርያ ስለሚሆን ነዉ። በአሁኑ ግዜ ብዙ ሰዎች በክፉ መንፈስ ፍራቻ ዉስጥ ወይንም ላደረጉት ክፉ ነገር ቅጣትን ወይንም መልሰዉ የሚከፍሉበትን ሁኔታ በማሰብ በፍራቻ ዉስጥ ነዉ የሚኖሩት።

ስለተፈጥሮ እና ሃጥያት ላይ ስለመዉደቅ መማር ሰለ ክፉ መንፈስ እና እግዚአብሄር በክፉ መንፈስ ላይ ስለአለዉ ስልጣን ጠንቅቀዉ እንዲረዱ ያግዛቸዋል። በኤድን ገነት የሆነዉን በተረዳን ግዜ ለብዙ ጥያቄዎቻችን መልስ እንዲሁም ለሰዉ ልጅ በግልጽ ተግዳሮት ለሆኑ የአለም ምልከታዎች ማብራርያ ለመስጠት ያስችለናል። ወደ ኤፌሶን ሰዎች ፪ ፡ ፫ የሰዉ ልጅ እንዴት በተፈጥሮው ሃጥያተኛ እንደሆነ እና በሮሜ ሰዎች፫፡፪፫ በተግባር ተብራርቱዋል። ወደኤፌሶን ሰዎች ፪፡፩-፩፫ እግዚአብሄር ሰዉን በሃጥያት ምክንያት በመንፈስ እንደሞተ አድርጎ እንደሚያሰበዉ ይጠቅሳል። ይህ ደግሞ ከእግዚአብሄር መነጠልን ያስከትላል። እግዚአብሄር ትክክለኛ ዳኛ በመሆኑ እያንዳንዱ

ሃጥያት ከቅጣት አያመልጥም። መጽሃፍ ቅዱስ በግልጽ እንዳስቀመጠዉ የሃጥያት ዉጤቱ ሞት ነዉ።

ሰይጣን እኛን ሊያታልለን እና እግዚአብሄርን እንዳናገኝ ሊከላከለን ይፈልጋል። ሰይጣን አዳምን እና ሄዋንን ሲያስታቸዉ እና ወደ ሃጥያት ሲመራቸዉ እግዚአብሄርን በመቃወም እና እግዚአበሄርን እንዳያምኑት በማበረታታት ነበር። ከዛን ገዜ ጀምሮ የሰዉን ለጆ እያሳተዉ ይኖራል። የሰይጣን ተጾእኖ በህይወታችን ዉስጥ ያስከተለዉ ያለመታዘዝን እና እግዚአብሄር ላይ የጠላትንት ስሜትን ነዉ። የማይታዘዙ ሰዎች በእግዚአብሄር የማዳን መንገድ ሳይሆን በራሳቸዉ ጥረት፣ ርህራሄ፣ ሃሳብ እና የአኗኗር ዘዴ ነዉ ህየሚያምኑት።፡ ያለመታዘዘ ዉጥሄቱ ከእግዚአብሄር ለዘላለም መለየት ነዉ (የዮሃንስ ራእይ 20:11-15)

ሃጥያት የሚለዉን ሃሳብ ሊያወሩብት በጣም የሚከብድ ነዉ። በተለይ ደግሞ እስከአሁንም ከእግዚአበሄር ለተለዩ ሰዎች ወይንም ግለሰቦች። ነገር ግን አድማጮቻችን የሃጥያትን አንገብጋቢነት ይረዱ ዘንድ ልናግዛቸዉ ግድ ይላል። ያን ግዜ በህይወታቸዉ ዉስጥ የእግዚአብሄርን አስፈላጊነት ይገነዘቡታል። ይህንን መልእክት በምናስተላልፍ ግዜ በጨዋነት እና በአክብሮት ሊሆን እንጂ እየከሰስን ወይንም በመጋፈጥ ስሜት መሆን የለበትም። እየሱስ የሰዉን ልጅ በከበሬታ እንዳስተማረዉ እና እንዳፈቀረዉ ሁሉ መልካሙን ዜና ለሌሎች በምናስተላለፍ ገዜ ይህንኑ አኪያሂያድ ልንጠቀም ይገባል።

አደማጮቻችን የሃጥያትን ችግር በጥልቁ ከተረዱት በሁዋላ መፍትሄ እንዳለዉ ልንነግራቸዉ ይገባል። እየሱስ ከሃጥያታችን ሊመልሰን እና ከሃጥያታችን ሊያድነን ሁሌም ይጓጓል። ሃጥያት የሚለዉ ሃሳብ በሚነሳ ገዜ ይህ በጣም አስፈላጊው ክፍል ነዉ። እየሱስ የመጣዉ ሁላችንን ሃጥያትን ተከትሎ ከሚመጡ ዉጤቶች ለማዳን እና የእግዚአብሄርን ስጦታ ( የዘላለም ህይወት ወደ ሮሜ ሰዎች 6:23) እንቀበል ዘንድ ነዉ። ይህ ስጦታ ሊቀበለዉ ለፈለገ ለማንኛዉም ሰዉ ከዚህ በፊት ያደረጉት ነገር ምንም ይሁን ምንም ክፍት ነዉ። መልካሙን ዜና በማመን ፣ ንስሃ በመግባት እና እየሱስን በዉስጣቸዉ ይኖር ዘንድ በመጋበዝ የሚሆን ነዉ።፡የህንን አስደሳች ዜና በደስታ ልናካፍለዉ ይገባል። ምንም እንኩዋን ሰይጣን ወደ ጥፋት ሊመራን ቢሞክርም እየሱስ መሃል በመግባት የምንደንበትን መንገድ ያዘጋጅልናል። ሃሌሉያ!

አድማጮቻችን የሃጥያትን አንገብጋቢነት ይረዱ ዘንድ ልናግዛቸዉ ግድ ይላል። ያን ግዜ በህይወታቸዉ ዉስጥ የእግዚአብሄርን አስፈላጊነት ይገነዘቡታል። ይህንን መልእክት በምናስተላልፍ ግዜ በጨዋነት እና በአክብሮት ሊሆን እንጂ እየከሰስን ወይንም በመጋፈጥ ስሜት መሆን የለበትም። እየሱስ የሰዉን ልጅ በከበሬታ እንዳስተማረዉ እና እንዳፈቀረዉ ሁሉ መልካሙን ዜና ለሌሎች በምናስተላለፍ ገዜ ይህንኑ አኪያሂያድ ልንጠቀም ይገባል።.

# ክለሳ

- የእግዚአብሄርን ትእዛዛት እንዳይቀበሉ በሰይጣን የተታለሉት አዳም እና ሕይዋን ሃጥያት ወደ ምድር እንዲገባ ምክንያት ሆኑ። የሰዉ ልጅ በሙሉ በሃጥያት ዉስጥ የተወለድን ብቻ ሳንሆን ሰይጣን በቀጣይነት ሃጥያትን እንሰራ ዘንድ ሲያስተን የምንኖር ነን።ነገር ግን መቀበል ለሚሹ በሙሉ እየሱስ መዳንን እንሆ ይላል።

- ወንጌልን በምትሰብክበት ገዜ ስለ ሃጥያት መናገረን አለመርሳት በጣም ጠቃሚ ነዉ። ይህ አድማጮቻችን እየሱስ ምን ያህል እንደሚያስፈልጋቸዉ ይረዱ ዘንድ ያግዛቸዋል። በተጨማሪም የዘላለማዊ ህይወት ሰጦታን ተቀባይ ያደርጋቸዋል።

- ስለሃጥያት አድማጮቻችን ግንዛቤዉ እንዲኖራቸዉ ማገዙ ጠቃሚ ሁኖ ሳለ መረጃዉን የምናስተላልፈበት መንገድ በፍቅር እንጂ ብመጋፈጥ ስሜት መሆን የለበትም። ክብር የሌለዉ ወይንም ዉንጀላን የተቀኘ ቋንቋ መጠቀም አድማጮችን ከዋናዉ እና ከጠቃሚዉ የ መዳን መልእክት እንዲርቁ ያደርጋቸዋል።

## ሃሳብህን ስጥብት

- መልካም ዜናን ክምትሰብክበት መንገዶች ጥቂቶቹ እንዴት ያሉ ናቸዉ? መልካም ዜናን በምትሰብክ ግዜ ልታነሳቸዉ ከምትፍልጋቸዉ አርእስቶች ጥቂቶቹን ምን ምንን ይስጠቃልላሉ?

- በስብከትህ ዉስጥ ልታካትታቸዉ የምትችለው ርእዮተ አለማዊ ተግዳሮቶች እንዴት ያሉ ናቸዉ?

- አማኝ ያልሆኑ ጓደኞችህ ዉንጀላን ሳትጠቀም ስለሃጥያታቸዉ ይበልጥ እንዲያስቡ የምታደርግበት ዘዴ እንዴት ያለ ነዉ?

በተለይ ካልተገለጸ በቀር፥ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓምከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ት ርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈ ቃድ ተቀድቶ የታተመ ነዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.